بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

# <u>በሲያትልና አካባቢዋ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በአንድነት በመሰባሰብ ያወጡት የጋራ መግለጫ</u>

Nov.19,2011 በኢማስ ማእከል ቁጥራቸው ከመቶዎች በላይ የሚገመት ህዝብ የተገኘበት ታላቅ የህዝበ ሙስሊም ስብሰባ ተካሂዶዋል። ይህን ያህል ህዝብም እንዲገኝ ያደረገው ዋናው ምክንያት የሁሉም የሆነ የጋራ እምነት በመነካቱ ነው፤ ሁሉም ብሄረሰብ የዘር የፖለቲካ እንዲሁም ሌላውን ጉዳይ ወደጎን በመተው ዋናና አንገብጋቢ የሆነውን የእምነቱን ጉዳይ በማስቀደም እንዳለ ለመምጣትና ለመወያየት ችሎዋል። በእለቱም በበድር ኢትይጵያ የተዘጋጀ ዶክመነተሪ ፊልም ታይቶዋል፤ ፊልሙም ብዙዎቹ ያነቡበትና የነቁበት እንዲሁም ይህ እስከመቼ? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ በያንዳንዱ አእምሮ የጫረ ታሪካዊ ፊልም ነበር። ቀጥሎም አቂዳን በተመለከተ በተለይም "ስለ አሕባሽ የጥመት አቅጣጫና አቂዳ" በ4 የተለያየ ቋንቋዎች ትምህርት በሰፊው ተሰጥቶዋል። ከቤቱም ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሰንዝሮዋል በተለይም ከህዝቡ የተሰነዘሩት አስተያየቶች የሁሉንም አእምሮ የነካና የቀሰቀሰ ነበር። ለአብነት የሚከተሉትን እንጥቀስ

" እኔ የኦሮሞ ዜጋ ነኝ ላለፉት 20 አመታት ከአማራውም ሆነ ከትግሬው ብሄረሰብ ጋር ቁጭ ብዬ ስለ ዲኔ (ሃይማኖቴ) የተወያየሁበት ጊዜ አላሰታውስም የዛሬ ደስታዬ ወደር የለውም ይህ እንግዲህ ጅምር ነው ተዋውቀናል ውህደታችንንና አንድነታችንን አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን አጥብቆ አሳስቦዋል" እንዲሁም ሌላኛው ተናጋሪ "ይህ ዛሬ በአገራችን ላይ ያንዣበበውና ሙስሊሙን ዑማ ለመበተን የመጣው የአሕባሽ ቡድን ላአንዴ አይደለም ለሁለተኛ ዙር ቢመጣም እንኳን ይበልጡን የእኛን አንድነት ከማጎልበቱና ከማጠንከሩ ባሻገር ምንም የሚያመጣው ነገር የለም ብሎዋል። እንዲሁም ከወንድም ከሴቱም ይህ አይነቱ ግንኙነት መቀጠል እንዳለበትና በዚህ አጋጣሚ የተገኘውም ትስስር መቋረጥ እንደሌለበት አሳስበዋል፤

በዚህ ስብሰባ የተለያዩ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበራት ተወካዮች ተገኝተው በኢትዮጵያ ውስጥ በሙስሊሞች እየተካሄደ ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ እና የሃይማኖት ጣልቃ ገብነት አውግዘዋል:: ስለተፈጠረው ችግርም በደንብ ከተወያዩ በኋላ ለወደፊት እንደ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ዜጋ መብትን ለማስጠበቅ በሚደረገው ማንኛውም ተሳትፎ በሃላፊነት እንዲመሩት ሁሉንም ማህበራት ያማከለ ከአስር ያላነሱ አባላት ያሉት የጋራ ኮሚቴ መስርተው ኮሚቴውም በሚያወጣው ማንኛውም

ዓይነት ውሳኔ  በሲአትል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በሙሉ በተግባር ለመተርጎም ቃል ገብተው ተለአያይተዋል።

## <u>የጋራ ኮሚቴውም የአቋም መግለጫ</u>

1) መንግስት በሃማኖቶች መሃል ጣልቃ ገብነቱን ያቁም። እንላለን

2) በሙስሊሞች ደምና ትግል የተገኘው መጅሊሳችን ህዝበ ሙስሊሙን በማይወክሉ ካድሬዎች ከሚመራ ይታቀብ። ሙስሊሙም ህገመንግስቱ በሚፈቅድለት መብቱ በመጠቀም የሚወክሉትን እንዲመርጥበት ግርዶሹ ይገፈፍ፤ ጣልቃገብነቱ ይቁም፤ የፍትህ በሩ ይከፈት፤ እንላለን!

3) መንገስት እፍኝ በማይሞሉና ምንነታቸው ካልታወቀው የአሕባሽ ቡድኖች ጋር መወገኑን ያቁም።እንዲሁም በህዝበ ሙስሊሙ ላይ “ ዋሃቢይ” የሚለው የስም ታርጋ ከመለጠፍ ይልቅ የዜጎቹን ህገ-መንግስታዊ መብት ያስከብር በማለት እናሳስባለን።

4) “አሕባሾች!” እስከዛሬ በሰላም የኖረውን የኢትዮጵያን ሙስሊም ማወክና ማሸበራችሁን አቁሙ። በማለት አጥብቀን እናሳስባችኋለን፤ እናስጠነቅቃችኋለን!

5) በስውርም ሆነ በማን አለብኝነተ በይፋ በሙስሊሞች ላይ የሚደረገው አፈና ፤ በትምህርት ተቋም ላይ የሚደረገው ሽረባና ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታ ማፈናቀል እንዲሁም ያለምንም መረጃ ማጎርና ማሰር ይቁም! ይብቃ እያልን አጥብቀን እናሳስባለን!

6) ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ተቻችሎ መኖር ብቻ ሳይሆን  እስከዛሬ ድረስ ችሎ ለመኖራቸው ብዙም መረጃ የማያስፈልገውና የማይጠይቅ ጸሃይ የሞቀው አገር ያወቀው ጉዳይ ነው በተለይም በአሁኑ ወቅት ችሎ ማለፉና

የደም ጠብታ አለማስከተሉ ፍራቻ ሳይሆን የዜግነት ግዴታ መወጣቱን አስመስክሮዋል። በመንግስት የሚረዳው የአሕባሽ ቡድን ግን ጠብቆት የነበረው የደም ጎርፍን ነው አሁንም እንደጣረ ነው። ይህ ደግሞ የአገሪቱን እርምጃ ከመነተቱ አልፎ ሁከትንና ሰላምን እንደሚነሳ ከወዲሁ እናሳስባለን። ለመቻቻል ወግ አለው ለመቻልም ገደብ አለው!!! መንግስት እንደመንግስትነቱ የዜጎቹን ህገመንጎስታዊ መብት ካላስጠበቀ በአሕባሽ ቡድንና እና ህገመንጎስቱን በመጣስ በሚበጠብጡ ግለሰቦች ሳቢያ በሚከሰቱት ማንኛውም ቀውስና ብጥብጥ እንዲሁም የደም መፋሰስ መንግስት ከተጠያቂነት እንደማያልፍ ከወዲሁ አጥብቀን ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን።

"አላህ  በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ ያመጣውን በላ ያንሳልን"

አሚን!

January 10,2012

የጋራ ኮሚቴው